# ለከትና ገደብ የሌለው የአማራ ህዝብ በደልና ግፍ ከቶ መቆሚያው መቼ ይሆን?

ጠባቂም ጠያቂም የሌለው ሆደ ሰፊው የአማራ ህዝብ፣የሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ችግር እየተፈራረቁበት፣ማንነቱንና ክብሩን ቢፈታተኑትም፣ያለ ማንም ድጋፍና አይዞህ ባይ፣የገጠመውን መከራ፣ አንጀቱን አስሮ፣ሲተኛም ተመስገን፣ ሲነሳም ተመስገን እያለ፣ ክፉ ቀንን እየተሻገረ እዚህ ደርሷል። አሁንም አማራው የገጠመውን ችግር ይወጠዋል።

አሁን በሰሜንና ደቡብ ወሎ የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ጥፋት በከፍተኛ ሁኔታ ተባብሶ አዝመራውን እያወደመ ህልውናውን አደጋ ላይ እየጣለው ይገኛል። ይህንን አደጋ የክልሉም ሆነ የአብይ አህመድ ኦነጋዊ ጥምር አስተዳደር እያዩ እንዳላዩ ጀርባቸውን ሰጥተውታል። ምክንያቱም አደጋው አማራ ላይ ነው። ነገር ግን ህገ መንግስት በሚሉት የቅራኔ ሰነዳቸው አንቀፅ 93 ንኡስ አንቀፅ 1ሀ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንደሚታወጅ ይገልፃል።

ነገር ግን ጦም እያደረ ታክስ በሚከፍለው የአማራ ገንዘብ፣ ደልቦ ላቱን እየወዘወዘ፣ በሴራና ክፋት የተጠመደው አብይ አህመድና ቡድኑ፣ባላቸው ፀረ አማራ ጥላቻ የተነሳ፣አማራውን በፖለቲካና በኢኮኖሚ አዳክሞና አቀጭጮ ለማጥፋት ፣ለያዙት ድብቅ አጀንዳ ይህን ድንገተኛ የአንበጣ መንጋ፣ እንደ ጥሩ አጋርና ተባባሪ ስለሚቆጥሩት፣ አንበጣው አደጋ፣ ከማድረሱ በፊት፣ለመቆጣጠር ፍላጐት ያላሳዩበት፣ዋና ምክንያት ይኸ እንደሆነ ለኔ ግልፅ ነው። ሌላው በዚሁ ህገ ወያኔ በአንቀፅ 93 ንኡስ አንቀፅ 1ለ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም፣የተከሰተበት ክልል አስተዳደር፣የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ እንደሚችልም ይናገራል።

ግን አማራው አለመታደል ሆኖ፣የተሸከመው ህይወት አልባው ብአዴን(አደፓ) የሚባል፣አሞት አልባ ድርጅት፣ ይኸ ህገመንግስታዊ ስልጣን እንዳለው አለማወቁ፣ ድርጅቱ በቁሙ ሞቶ ህዝቡንም ይዞት እየሞተ እንደሆነ ያሳያል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አስፈላጊነት ህዝቡን አስተባብሮ በባህላዊ መንገድም፣ በኤሊኮፍተርም የታገዘ ርብርብ በማድረግ ፣ ካስፈለገም ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ የኤሊኮፍተር እርዳታ ጠይቆ አደጋውን ለመቆጣጠር ነው።

ግን የአብይ አህመድ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የህዝብ ህይወትና ንብረት ለመጠበቅ ሳይሆን፣ ለስልጣን መጠበቂያ ዋና የአፈናና የግድያ መዶሻ ስለሆነ፣ውሀ ሲሉት እርጐ የሚሰጠው የወሎ ገበሬ ችግር ለአብይ አህመድና ለቡድኑ አላሳሰባቸውም። ግን ገበሬው ከሌለ መኖር እንደማይችሉ በማያውቁ ነፋስ አመጣሾች ሀገራችን መመራቷ ለሁላችንም እፍረት ነው። ወገኔ ፈጣሪ ብቻ ከጭንቅ ያውጣህ።

ክብር ለኢትዮጵያ!!!

አብዱ አሊ

2019-11-07